# ስለ ገና በዓል እና ጾም አንዳንድ ጥያቄዎች

የገና እና የጥምቀት በዓላት ሲደርሱ በምእመናኑ ዘወትር የሚጠየቁ ጥያቄዎች አሉ። እነዚህን እና መሰል የሕዝቡን የዘወትር ጥያቄዎች መልስ የያዘ የማያዳግም ጥራዝ ማውጣት ከሊቃውንት ጉባኤ የሚጠበቅ ነው። አብዛኞቹ ጉዳዮች አበው ቀድመው ሥርዓት የሠሩባቸው እና ማብራርያ ብቻ የሚያስፈልጋቸው ናቸውና። ለዛሬ ሦስቱን ብቻ እንመልስ።

ገና እና ጥምቀት ዓርብ እና ረቡዕ ቢውሉ ይበላባቸዋል ወይስ ይጾማሉ?

ፍትሐ ነገሥት፡ ዳግመኛ በየሳምንቱ ዓርብ እና ረቡዕን መጾም ነው። በዓለ ሃምሳ፣ የልደት እና የጥምቀት በዓል የተባበሩባቸው ጊዜ ካልሆነ በቀር /ዐንቀጽ 15፣ ቁ 566/

የዓርብን እና የረቡዕን ጾም ግን ከልደት፣ከጥምቀት እና ከበዓለ ሃምሳ በቀር ዘወትር ይጹሙ /ዐንቀጽ 15፣ቁ 603/

የገና እና የጥምቀት ቅዳሴ ስንት ሰዓት ነው?

ፍትሐ ነገሥት፡ ስለ ልደት እና ጥምቀት ግን በዚያ ዘመን በኒቂያ የተሰበሰቡ ሊቃውንት ቅዳሴው በሌሊት ይሆን ዘንድ አዘዙ /ዐንቀጽ 15፣ ቁ 595/

ልደት ጋድ አለው?

ፍትሐ ነገሥት፡ የልደት እና የጥምቀት በዓላት ጋድ አላቸው /ዐንቀጽ 15፣ ቁ 566/

ትንታኔ፡ የገና ጾም 44 ቀናትን ይይዛል።

40 ጾመ ነቢያት

3 ጾመ አብርሃም ሶርያዊ

1 ጋድ

ድምር 44

የገና ጋድ ከጾሙ ተያይዞ የተቀመጠ እንጂ ለብቻው የተቀመጠ አይደለም። ለምሳሌ ሰሙነ ሕማማት ለብቻው የሚቆጠር ጾም ነው። /ዐንቀጽ 15፣ቁ 565/ ነገር ግን አንድ ሰው ዐቢይ ጾምን ሳይጾም ከርሞ ሕማማትን ለብቻው መጾም አይችልም። የገናም ጋድ እንዲሁ ነው።

ይህንን ጋድ የልደትን ጾም የማይጾሙ ሰዎች እንዲጾሙት የተሠራ ነውን?

መልስ፡ በቤተ ክርስቲያን ላልተጠመቁ፣ ለማይቆርቡ፣ ንስሐ ለማይገቡ፣ ለማያስቀድሱ፣ ለማይጾሙ ሰዎች ተብሎ የተሠራ ልዩ ሥርዓት የለም። በፍትሐ ነገሥት ዐንቀጽ 15፣ ቁ 565 እንደተገለጠው ሰባቱ አጽዋማት «ለክርስቲያን ሁሉ» የታዘዙ ናቸው። ስለዚህም የገናን ጾም ክርስቲያን ሁሉ ጾመው በበዓለ ልደት ሊገድፉ ይገባቸዋል። ፍትሐ ነገሥት ስለ ገና ጾም ሲገልጥ «መጀመርያው የኅዳር እኩሌታ ፋሲካው የልደት በዓል ነው» ይላል /ዐንቀጽ 15፣ ቁ 568/። ይህም ከገና ጾም ተሸርፎ የሚጾም ነገር እንደሌለው ያሳያል።

መልካም በዓል

Email This BlogThis! Share to Twitter Share to Facebook Share to Google Buzz

Posted by ዳንኤል ክብረት

**3 comments:**

aron said...

Thank You D/N daniel i read something else on another website that no matter what we should always fast wed and fri except on beale amsa. Now i know the truth from Fitha Negest thank you for explaining this clearly. God bless your service.

January 5, 2011 10:02 PM

Anonymous said...

Thank you.d/n daniel.
i was confusing .but i get the right answer. GOD BLESS U MELKAM GENA

January 5, 2011 11:19 PM

Anonymous said...

Thank you so much for this quick answer. I specially appreciate your citing of the reliable source, i.e., Fitiha Negesit.

I wish you would have added or asked someone to say a bit about how the Kidasse is celebrated. I mean, when will it start and will finish.

Thank you so much and may God bless you.

Orthodox child

January 6, 2011 2:23 AM